# በትምህርት ቤት የግላዊነት ፖሊሲ

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች - ለወላጆች

በትምህርት ቤት ተማሪዎቻችንን ለማስተማርና ለመርዳት ዋና ድርጊቶችን ለማሟላት ሲባል የተማሪዎችን መረጃ ለሌላ ስለማካፈል እንዲቻል በትምህርት ቤት የግላዊነት ፖሊሲ በኩል ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ ያሳውቃል።

የትምህርት ቤት የግላዊነት ፖሊሲ ‘ማወቅ ለሚያስፈልግ’ የአሰራር መዋቅር ግልጽ ያደርጋል፤ ይህም የትምህርት ቤት ሰራተኛ እንደ የሥራ አካል መሆን መጠን ስለ ተማሪዎች መረጃ ማወቅ ከሚያስፈልገው ሌላ ሰራተኛ ጋር በጋራ ይጠቀማሉ። ይህ ከቪክቶሪያ የግላዊነት ህግ ጋር ተመሳሳይ ነው።

## ፖሊሲው ለማን ነው የሚመለከተው?

ፖሊሲው ተግባራዊ የሚሆነው ለሁሉም ማእከላዊ ክልል እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ማለት ለርእሰ መምህራን፤ ለአስተማሪዎች፣ አስተማሪዎችን ለሚጎበኙ፣ ለማሕበራዊ ሰራተኞች፣ ለነርሶች፣ ለተማሪ ድጋፍ አገልግሎት ሀላፊዎች (SSSOs) እና ለሌላ ተባባሪ የጤና ባለሙያዎችን በሙሉ ያካትታል። ይህ ማለት ከዚህ በታች ያለው ለሁሉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ‘ስለማወቅ የሚያስፈልግ’ አስራር መዋቅር ተግባራዊ እንደሚሆን፤ ይህም ተቀጣሪዎች፤ አገልግሎት አቅራቢዎች (ኮንትራክተሮች) እና ለመምሪያው ተወካዮች (ክፍያ ለሚያገኝ ወይም ለማይከፈለው) ያካትታል።

## ማወቅ የሚያስፈልግ

ትምህርት ቤቱ ከዚህ በታች ያሉትን ማካሄድ እንዲችል ሁሉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስለ ተማሪው ያለውን መረጃ ‘ማወቅ ከሚያስፈልገው’ ሌላ ሰራተኛ ጋር መጠቀም መቻል እና ማካፈል እንዳለበት:

1. ተማሪን **ማስተማር** (ለግለሰብ ፍላጎት እቅድ ማውጣት ወይም ለመማር እንቅፋት የሚሆኑትን ማቅረብ ያካትታል)
2. በተማሪ ማሕበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነትና ጤንነት ላይ **ድጋፍ መስጠት**
3. **ህጋዊ** ግዴታዎችን ማሟላት፤ በዚህ የሚካተት:
   - በተማሪው፤ በሌሎች ተማሪዎች፤ በሰራተኛ ወይም በጎብኝዎች (ሀላፊዎች) ላይ በሃይለኝነት የሚከሰተውን የአደጋ ጉዳት ለመቀነስ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ
   - ለአካለ ጉዳተኛ ተማሪዎች (በጸረ-አድልዎ ፈጠራ ህግ) ተገቢውን ማስተካከያ ለማካሄድ
   - ደህንነቱ የተጠበቀና ድህና የሥራ ቦታን (ለሥራ ጤና ጥበቃና ደህንነት ለተጠበቀ ህግ) ለመፍጠር ነው።

## ማን ‘ማወቅ እንዳለበት’ የሚወስነው ማን ነው?

የርእስ መምህሩን መመሪያ ተመርኩዞ ማን የተለየ ፍላጎት እንደሚያስፈልገው ለማወቅ፤ ስለ ተማሪው ጠቃሚ መረጃ፤ ‘በፍላጎት ማወቅ’ የአሰራር መዋቅር መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ ሰራተኛ አባል ይወስናል።

‘ማወቅ ከሚያስፈልገው’ ሌላ ሰራተኛ ጋር ጠቃሚ መረጃን አብሮ መጠቀም ከመደበኛ ንግግር ወይም ሀሜት ጋር በጣም የተለየ ነው።

ስለ ተማሪዎች ጥልቀት ያለውን ጠቃሚ መረጃ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለማወቅ ይፈልጋሉ። ሰራተኞች እንደዚህ ያሉትን የግላዊና የጤና ስሜት ቀስቃሽ መረጃዎች በሙሉ በክብር ማስተናገድ እንዳለባቸው፤ እንዲሁም ‘ማወቅ ከሚያስፈልገው’ ባሻገር ለሌላ አካል አውጥቶ አለመስጠት።

## ለቀጣዩ የቪክቶሪያ መንግሥት ትምህርት ቤት ስለ ተማሪ ምን ዓይነት መረጃ እና መዝገብ ማስተላለፍ ይቻላል?

አንድ ተማሪ ለሌላ የቪክቶሪያ መንግሥት ትምህርት ቤት ፈቃደኛ በሚሆንበት ጊዜ፤ አሁን ያለበት ትምህርት ቤት ስለ ተማሪው ግላዊና ጤንነት መረጃ ለቀጣዩ ትምህርት ቤት ማቅረብ ይችላል።

ይህ ከዚህ በታች ባለው ማንኛውም ወይም በሁሉም መንገዶች ላይ ሊፈጠር ይችላል:

- በቃል ንግግር: ርእሰ መምህር ከርእሰ መምህር ጋር (ወይም ሥልጣን ካለው ተወካይ ጋር)።
- በወረቀት: የተማሪውን ሪኮርድ መዝገብ ቅጂውን ለቀጣዩ ትምህርት ቤት በማቅረብ (ማንኛውም የጤና ሪፖርት ያካተተ)።

- በኤሌትሮኒካል: በ CASES21 ማስተላለፊያ አሰራር፤ የተማሪ በመስመር ላይ ጉዳይ አሰራር ዘዴ (SOCS) እና/ወይም በኢሜል በኩል መላክን ያካትታል።

‘ማወቅ በሚያስፈልገው’ የአሰራር መዋቅር መሰረት ለቀጣዩ የቪክቶሪያ መንግሥት ትምህርት ቤት ምን ዓይነት መረጃ እንደሚቀርብ በርእሰ መምህራን (ወይም ስልጣን ባላቸው ተወካዮች) በኩል ይወሰናል:

*ተማሪን በተገቢው ለማስተማር ወይም ለመደገፍ እና የትምህርት ቤት ህጋዊ ግዴታን ለማሟላት ቀጣዩ ትምህርት ቤት ‘ማወቅ የሚያስፈልገው’ ምን መረጃ ነው?*

## ‘ማወቅ ለሚያስፈልግ’ የአሰራር መዋቅር

### ተግባራዊ ሃላፊነት

ለተማሪዎች በትምህርት ቤት ተግባራዊ ሃላፊነት ማለት በተማሪ ባህሪ፤ አካል ጉዳት፤ የቤተሰብ ሁኔታዎች ወይም ከተማሪው ጋር በተዛመደ ሌላ ማንኛውም ሁኔታዎች ሳቢያ **ለሆነ ሰው** ማንኛውም **በሃይለኝነት የአደጋ ጉዳት** ስለመፍጠር ተግባር የርእሰ መምህር ወይም ሌላ የአመራር ቡድን አባል ማወቅ ይኖርበታል።

ስለዚህ፤ ለምሳሌ፡ ተማሪው ከዚህ በታች ባሉበት ምክንያት በሆነ ሰው ላይ ተግባራዊ የሆነ ማንኛውም በሃይለኝነት ችግር ከተፈጠረ:

- ጠበ ጫሪነት ባህሪ ማሳየት
- የችግር ሰለባ ለመሆን ወይም ለመደባደብ፣ መጣላት ወይም በእድሜ እኩያ ካልሆነ ጋር ወሲባዊ የሆነ ባህሪያት ማሳየት
- ስሜታዊ፣ ድህንነት ወይም እራስን- ስለመጉዳት ችግሮች ከተፈጠረ

ከዚያም ሰራተኛው **ለርእሰ መምህሩ** (ወይም በትምህርት ቤት አመራር ቡድን ለሆነ ሌላ አባል) **መናገር** አለበት።

ከዚያ በኋላ የርእሰ መምህሩ ያሉትን ቋሚ መረጃዎችን ማወቅ ላለበት ሌላ ሰራተኛ አባል ያካፍላል ምክንያቱም እነዚህ ሰራተኞች ማወቅ ያለባቸው ከተማሪ ጋር ስለሚሰሩ ወይም ስለሚቆጣጠሩ ነው። ርእሰ መምህሩ ያለባቸውን ሃላፊነት በብቃት ለመወጣት፤ ሰራተኞች ያላቸውን ጠቃሚ የሆኑ በቂ መረጃዎች ለርእሰ መምህሩ ማቅረብ አለባቸው – ስለዚህ ርእሰ መምህሩ ያለባቸውን የእንክብካቤ አቅርቦት ሃላፊነት ማሟላት እንደሚችሉም ነው።

ተግባራዊ የሆነ በሃይል አደጋ ጉዳት ከደረሰ፤ ሰራተኛው በዚያን መረጃ ተመርኩዞ እርምጃ መውሰድና ምንም እንኳን ተማሪ ወይም ወላጅ መረጃው እንዳይወጣ ቢጠይቁም ያለውን መረጃ ‘ማወቅ ከሚያስፈልገው’ ሌላ ሰራተኛ ጋር አብሮ መጠቀም ይኖርበታል።

### የጸረ-አድልዎ ፈጠራ ህግ

አካለ ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች (በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ፕሮግራም መሰረት ቢፈቀድላቸውም ወይም ባይፈቀድላቸው) **ተገቢ የሆነ ማስተካከያ** ለማቅረብ የትምህርት ቤቱ ግዴታ ሲሆን ይህ ማለት ስለ ተማሪው የአካል ጉዳተኛ መሆን ጠቃሚ መረጃ ማግኘትና ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች ከተማሪው ጋር ለሚሰራ ወይም ከሚቆጣጣር ሰራተኛ ጋር አብሮ በጋራ መጠቀም አለባቸው።

ምን ዓይነት ማስተካከያ ተገቢ ስለመሆኑ፤ ትምህርት ቤቱ በትክክል ውሳኔ ማካሄድ እንዲችል ይህን ማካሄድ ያስፈልጋል፤ ከዚያም እነዚህን ማስተካከያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

እንዲሁም የእንክብካቤ ሃላፊነትን ለዚያ ተማሪ ለማሟላት ያስፈልግ ይሆናል (ለምሳሌ፡ የጤና ችግር ያለበት ተማሪ ህክምና ያስፈልገው ይሆናል)።

ይህ ማለት ከዚህ በታች ያሉትን ማድረግ እንዲቻል፤ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ከተማሪው ጋር አብሮ የሚሰራ ወይም የሚቆጣጠር ሌላ ሰራተኛ ጋር አብሮ በጋራ መጠቀም:

- የተማሪውን አካል ጉዳት ለመረዳትና በትምህርታቸው እና በማሕበራዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነት ላይ እንዴት ችግር እንደሚፈጥር ለመረዳት
- በትምህርት ቤት ውስጥ ተገቢውን ማስተካከያ ተግባራዊ ለማድረግ፤ ይህም በተማሪዉ ህክምና አቅራቢ ሙያተኞች የቀረበውን ምክር በሙሉ ለመረዳት ይሆናል።

## የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከወላጆች ጋር ሲሰሩ፤ ማለት እንደ የደህንነትና የባህሪ ፖሊሲዎች፤ ጠቃሚ የሆኑትን የትምህርት ቤት ፖሊሲዎች ይከተላሉ። ጠቃሚ የሆኑ ፖሊሲዎችን ለማግኘት ወደ የርስዎ ትምህርት ቤት ድረገፅ ገብቶ ማየት።

## ስለ ትምህርት ቤት ፖሊሲዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘትና ግላዊ የሆኑ መረጃዎችን ለመቆጣጠር የትምህርት ቤት ሰራተኛን ማነጋገር ወይም በትምህርትና ስልጠና መምሪያ ለግላዊነት ሀላፊ/DET Privacy Officer በኢሜል፡ privacy@edumail.vic.gov.au ማነጋገር።